# የገንዘብ ሚኒስቴር

## መመሪያ ቁጥር 1004/2016

# የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርአትን ለመወሰን የወጣ

ሰኔ 2016 ዓ.ም

Uploaded on the website of the Ministry of Finance on 12 June 2024.

# የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1004/2016

የኤክሳይዝ ታክስ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ፣ ህገወጥ ንግድን ለመከላከል፤ እና የህዝብ ጤና እና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ዲጂታል እና አካላዊ የኤክሳይዝ ቴምብርን ስራ ላይ ማዋል ከፍተኛ እገዛ የሚኖረው በመሆኑ፣

የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ስርአትን ለማዘመን፤የኤክሳይዝ ታክስ ህጎች እንዲከበሩ ለማድረግ፤ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ምርት እና ስርጭት ለመከታተል የሚያስችል የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2018 (በተሻሻለው) አንቀጽ 29 እና 42 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1004/2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) “ስልጣን የተሰጠው ሰው” ማለት በታክሱ ባለስልጣን የበላይ ሃላፊ ወይም በበላይ ሃላፊው ስልጣን በተሰጠው ሰው በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ማናቸውንም ተግባር እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤
2) “የጥቅል ማሸጊያ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ከአንድ በላይ ጥቅሎችን የሚይዝ ማሸጊያ ነው፡፡

3) “መገልገያ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የሚመረቱበት፣ የሚከማቹበት ወይም ለገበያ የሚቀርቡበት ማናቸውም ስፍራ፣ ህንጻ ወይም የሽያጭ መሳሪያ ነው።

4) “የተዘጋጀ የአልኮል መጠጥ” ማለት ለመጠጥነት እንዲውል የተዘጋጀ እና ለችርቻሮ ገበያ የሚቀርብ የአልኮል መጠጥ ነው፤

5) “የኤክሳይዝ ቴምብር” ማለት በአካላዊ፣ በዲጂታል ወይም በሌላ ሚኒስቴሩ በሚወስነው መልክ የተዘጋጀ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ቴምብር ነው፤

6) “አስመጪ“ ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ወደአገር ለማስገባት በታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበ አስመጪ ነው፤

7) “አምራች” ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

8) “መያዣ” ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ለጅምላ ወይም ለችርቻሮ ሽያጭ በሚቀርቡበት ጊዜ የሚታሸጉበት ፓኬት፣ ጠርሙስ፣ ወይም ተመሳሳይ መያዣ ነው፤

9) “ኩባንያ” ማለት ለዲጂታል ቴምብር የተለየ መለያ ለመስጠት፣ የኤክሳይዝ ቴምብርን በተዋሃደ ስርአት ለማተም እና ለማከፋፈል እና የአስተዳደር ስርአቱን ለማልማት፤ለመትከል፣ ለማቀናበር፣ ለመሞከር፣ ድጋፍ ለማድረግ እና ለመጠገን በታክሱ ባለስልጣን ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

10/ “የአስተዳደር ስርዓት” ማለት የኤክሳይዝ ቴምብርን፣የምርት ሂሳብ አያያዝ ስርአትን እና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሶፍትዌሮችን እና ሃርድዌሮችን የሚይዝ የክትትል እና የቁጥጥር ስርአትን ያካተተ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የአስተዳደር ስርአት ነው።

11/‘የታክስ ባለስልጣን” ማለት እንደአግባብነቱ የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፤

12/ “አግባብነት ያለው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች፤ አስመጪ፤ ጅምላ ሻጭ ወይም አከፋፋይ ነው፡፡

13/ “የተለየ መለያ” ማለት አሃዛዊ ወይም ፊደል እና አሃዝን ያጣመረ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ፤ የሚከማቹ ወይም በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል አንድ የተለየ ኮድ ነው፡፡

14/ “አዋጅ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012( እንደተሻሻለ) ነው፤

15/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላት እና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ኤክሳይዝ ቴምብር

### 3. የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፍባቸው እቃዎች

1) የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሲመረቱ ወይም ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የተለየ መለያ የያዘ የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል፤

   ሀ) የአልኮል መጠጦች፤
   
   ለ) አልኮል እና አልኮል አልባ ቢራ፤
   
   ሐ) የወይን ጠጅ ወይም የተጣራ አልኮል የታከለበት ወይን ጠጅ እና ተመሳሳይ የአልኮል መጠናቸው ከ0.5% በላይ የሆነ ምርቶች፤
   
   መ) ለሰው መጠጥነት የሚውሉ እና ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረቱ መጠጦች (ከዚህ በኋላ “ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ መጠጦች” ተብለው የሚታወቁ) በውስጣቸው እንደ ስኳር፤ የፍራፍሬ ጭማቂ፤ የአትክልት ጭማቂ፤ የተፈጥሮ ወይም አርተፊሻል ጣእም ሰጪ ነገር፣ ውሃ፤ የሚኒራል ውሃ፤ ቅጠላ ቅጠል፤ቅመማ ቅመም እና ሌሎች ከአትክልት የሚገኙ ነገሮች ወይም ካርቦንዳዮክሳይድ

የተጨመረባቸው እና የአልኮል መጠናቸው ከ0.25 ያላነሰ የአልኮል መጠጦች፤

ሠ) ሲጋራ፣ ትምባሆ፣ በራስ የተጠቀለለ ትንባሆ፣ የሲጋራ ወረቀቶች፣ ቢዲስ፣ ክሬቴክስ፣ ጭስ የሌለው ትምባሆ፣ ሲጋራ፣ ሺሻ፣ የቧንቧ ትምባሆ እና ሌሎች የሚቃጠሉ ወይም የማይቃጠሉ የትምባሆ ምርቶች በሙሉ ለሰው ልጅ ፍጆታ ሲጋራ እና ሌሎች የትምባሆ ውጤቶች፤

ረ) የታሸገ ውሃ እና

ሰ) ከአልኮል መጠጥ ጋር የሚደባለቁትን ጨምሮ (ከዚህ በኋላ " አልኮል የሌለባቸው ስኳር በማጣፈጫነት የተጨመረባቸው መጠጦች" ተብለው የሚታወቁ) አልኮል የሌለባቸው መጠጦች፤ ካርቦን የተጨመረባቸው መጠጦች እና ጣፋጭነት ያላቸው መጠጦች፤

2) ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲለጠፍባቸው ሊወስን ይችላል፡፡

3) የታክሱ ባለስልጣን በእያንዳንዱ ምድብ ወይም ንኡስ ምድብ ውስጥ በሚገኝ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ ላይ የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር አይነት፣ ይዘት እና የሚለጠፍበትን አኳኋን ይህ መመሪያ ከጸናበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 4. የኤክሳይዝ ቴምብር ተፈላጊ ባህርያት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚለጠፈው ማናቸውም አይነት የኤክሳይዝ ቴምብር የሚከተሉትን ተፈላጊ ባህሪያት የሚያሟላ መሆን አለበት፤

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት የተለየ መለያ ያለው፤
2) አስመስሎ መስራትን መከላከል የሚያስችል፤
3) በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የኤክሳይዝ ቴምብርን እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች መከታተል የሚያስችል፤
4) የተመረቱ ወይም ወደ አገር የገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ምርት ሂሳብ መከታተል የሚያስችል፤
5) በእቃዎች ላይ የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ትክክለኛነት በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያለ ማናቸውም ሰው እንዲያረጋግጥ የሚያስችል፤ እና

6) ሲጋራ እና የትምባሆ ውጤቶችን በሚመለከት የአለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ምርቶችን ህገወጥ ንግድ ለመከላከል ባወጣው ፕሮቶኮል አንቀጽ 8 የተጠቀሰውን ምልክት፤

## 5. የተለየ መለያ ተፈላጊ ባህርያት

1/ የተለየ መለያ በአለምአቀፍ የደረጃዎች ድርጅት/ የአለም አቀፍ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ኮሚሽን ቁጥር 15459-2:201 ደረጃ ማሟላት አለበት።

2/ የተለየ መለያ ለታክሱ ባለስልጣን ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

3/ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ አግባብነት ያለው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ የተዘረጋውን የተለየ መለያ ስርአት በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚኖራቸውን እንቅስቃሴ በስርአቱ ውስጥ መመዝገብ አለበት።

4/ የታክሱ ባለስልጣን በራሱ ምርጫ የተለየ መለያ የማዘጋጀት ተግባር ለዚሁ አላማ በታክሱ ባለስልጣን በሚመደብ ገለልተኛ የሆነ ሶስተኛ ወገን እንዲከናወን ውክልና ሊሰጥ ይችላል (ከዚህ በኋላ “መለያ ሰጪ” ተብሎ የሚጠራ)።

5/ የመለያ ቁጥር ሰጪው መለያው የተለየ መሆኑን እና የተለየ መለያ የማዘጋጀቱ የስራ ሂደት፤ ፕሮቶኮሉ እና አሰራሩ በከፍተኛ ሚስጥር የሚጠበቅ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

6/ የተለየ መለያ የሚጠይቁ አምራች እና አስመጪዎች መለያ ሰጪው መለያውን መስራት እንዲችል አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መስጠት አለባቸው።

7/ የታክሱ ባለስልጣን ለአንድ ምርት የሚሰጠው የተለየ መለያ ሊኖረው የሚገባውን የአሃዝ እና ፊደል ብዛት ይወስናል፤ ለመለያ ሰጪው ያሳውቃል።

8/ የታክሱ ባለስልጣን በመረጃ ማከማቻ ስርአቱ ውስጥ የተቀመጠውን መረጃ ሳያይ የተለየ መለያውን መክፈት እንዲችል መለያ ሰጪው መረጃውን ሁለት ቋት ባለው የመረጃ ማከማቻ

ውስጥ ማስቀመጥ አለበት፡፡ የሁለቱ ቋቶች መጠን አግባብ ያላቸው የታክሱ ባለስልጣን ሰራተኞች ከኢንተርኔት መረብ ውጪ ሆነው መረጃውን ወደመገልገያ መሳሪያቸው በማውረድ የተለየ መለያውን ማንበብ በሚያስችላቸው ደረጃ በሚኒስቴሩ እና በመለያ ሰጪው መካከል በሚደረገው ውል ሊወሰን ይገባል፡፡

9/መለያ ሰጪው ሁሉንም መያዣዎች መከታተል እና መቆጣጠር እንዲቻል በካርቶኖች፤ በጥቅል መያዣዎች ወይም በማንቀሳቀሻ የእንጨት ርብራቦች እና በመሳሰሉት ላይ ምልክት ለማድረግ እና ጠቅላላውን የማሸጊያ ብዛት ለመመዝገብ የሚያስችል ስርአት ያዘጋጃል፡፡

10/ አግባብነት ያለው የኤኮኖሚ አንቀሳቃሽ የጥቅል መያዣ አማራጭን ለመጠቀም የሚፈልግ መሆኑን ካስታወቀ መለያ ሰጪው የዚህ አይነቱ የጥቅል መያዣ፤ የጥቅል መያዣ የተለየ መለያ እንዲኖረው እና ከጥቅል መያዣው በታች መጠን ያላቸውን ጥቅሎች በመጨረሻም በጥቅሉ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ማሸጊያ የያዘውን ብዛት ለይቶ ማወቅ የሚያስችል ምልክት መኖሩን እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለበት፡፡

11/ መለያ ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 10 ከተመለከተው በተጨማሪ የአለም የጤና ድርጅት የትምባሆ ውጤቶችን ህገወጥ ንግድ ለመከላከል ባወጣው ፕሮቶኮል አንቀጽ 8 የተመለከተው የመመዝገብ ግዴታ መከበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

12. ማናቸውንም ግዢ እንዲሁም እቃው ከአምራቹ ወጥቶ ከአምራቹ ጋር ግንኙነት እስከሌለው የመጀመሪያው ደንበኛ ድረስ የሚጓጓዝበትን መስመር በትክክል መከታተል እንዲቻል መለያ ሰጪው አግባብነት ላለው የኤኮኖሚ አንቀሳቃሽ የመለያ ኮድ እና ለመገልገያው የመለያ ኮድ መስጠት አለበት፡፡

13. መለያ ሰጪው የተለየ መለያው የማከማቻ ስርአት የተለያዩ ክፍሎች እርስ በርሳቸው መረጃን መለዋወጥ የሚችሉ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም የቴክኒክ ባህሪያትን ዝርዝር በሚመለከት የባለቤትነት መብት ጥያቄ በማያስነሳ አኳኋን ግልጽ ደረጃ መስጠት አለበት፡፡

14. ተተኪ አገልግሎት ሰጪ መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ አዲስ መለያ ሰጪ እስከሚመደብ ድረስ ለአገልግሎቱ ቀጣይነት ዋስትና መስጠት እንዲቻል መለያ ሰጪው ተግባራዊ ሊሆኑ የሚገባቸውን የአሰራር ስርአቶች የሚያሳይ የመውጫ እቅድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

15/ የተለየ መለያው የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ መሆን አለበት፦

ሀ) ምርቱ የተመረተበትን ቦታ፤
ለ) የማምረቻውን ስም፤
ሐ) የምርቱን አይነት፤
መ) ምርቱን ለችርቻሮ ገበያ ለማዋል የታቀደውን ቦታ፤
ሰ) ምርቱ የሚጓጓዝበትን መስመር፤
ረ) የሚቻል እስከሆነ ድረስ የአስመጪውን ስም

16/ የታክሱ ባለስልጣን ይህ መመሪያ ከጸናበት አንስቶ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ የተለየ መለያ የሚሰጥበትን አኳኋን የሚያሳይ ዝርዝር የሚወስን መመሪያ ያወጣል፤ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት ይህ ዝርዝር ወቅታዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 6. ለኤክሳይዝ ቴምብር የሚፈጸም ክፍያ

1) አምራቹ ወይም አስመጪው በሚያስፈልገው በእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት እቃ ላይ በሚለጠፈው የኤክሳይዝ ቴምብር ልክ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የማስከፈያ ሰንጠረዥ በተመለከተው የማስከፈያ ዋጋ ተመን መሰረት ለኩባንያው ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

2) ኩባንያው በዚህ መመሪያ አንቀጽ (3) መሰረት የኤክሳይዝ ቴምብር የሚያወጣው ወይም የሚያትመው የታክሱ ባለስልጣን ከኩባንያው ጋር በሚፈረመው ውል ስምምነት በሚደረስበት የአሰራር ስርአት መሰረት የተለየ መለያውን አግባብነት ያለው ምድብ ሲያጸድቅ ፡፡

3) ለኤክሳይዝ ቴምብር ክፍያ የሚፈጸመው አምራቹ ወይም አስመጪው የኤክሳይዝ ቴምብሩን ከመረከቡ ቢያንስ ከ15 ቀናት በፊት ነው፡፡

## 7. የኤክሳይዝ ቴምብር ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1) የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው እንደሚገባ የተለዩ እቃዎችን የሚያመርት ወይም ወደአገር የሚያስገባ አምራች ወይም አስመጪ የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲሰጠው በጸደቀው ቅጽ ለባለስልጣኑ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡ የታክሱ ባልስልጣን የማመልከቻውን ቅጽ እና ማመልከቻው የሚቀርብበትን ስርአት በመመሪያ ይወስናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከሚመረትበት ወይም ወደአገር ከሚገባበት ቀን ቢያንስ 60 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አምራች ወይም አስመጪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለኤክሳይዝ ቴምብር የሚከፈለውን ክፍያ ለኩባንያው መክፈል አለበት፡፡

4) ማናቸውም አስመጪ ወደአገር በሚያስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚለጠፍ የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲሰጠው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ እቃዎችን ወደአገር የሚያስገባ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት፡፡ የታክሱ ባለስልጣን ይህ መመሪያ ከጸናበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፍበትን አኳኋን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም የታክሱ ባለስልጣን አስመጪው የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ እቃዎችን ወደአገር የሚያስገባ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታውን ሳይወጣ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ግዴታ እንዲገባ በማድረግ የኤክሳይዝ ቴምብሩን እንዲያገኝ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

6) የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ መሰረት የተሟላ ማመልከቻ በቀረበለት በ5 የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በማመልከቻው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

7) የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ ምርቶችን የሚያመርቱ ወይም ወደአገር የሚያስገቡ ታክስ ከፋዮችን ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፡፡

## 8. የኤክሳይዝ ቴምብር ፍጆታን አስቀድሞ ስለማስታወቅ

የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራች እና አስመጪ ቢያንስ የኤክሳይዝ ቴምብሩን ከሚፈልግበት ወር የመጀመሪያ ቀን በፊት ካሉት 60 ቀናት በፊት ለስድስት ተከታታይ ወራት በየወሩ የሚያስፈልገውን ዲጂታይዝድ የተለየ መለያ ወይም የኤክሳይዝ ቴምብር ብዛት ግምት እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 9. ኩባንያን ስለመምረጥ

1) በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና አዋጁን መሰረት በማድረግ በወጡ መመሪያዎች ለግዢ አፈጻጸም የተዘረጋውን ስርአት በመከተል ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ኩባንያ ይመርጣል፤

   ሀ) የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው ቦታ ተፈላጊውን የአስተማማኝነት እና የደህንነት ደረጃ የሚያሟላ የተለየ መለያ ማውጣት የሚችል ስርአት የሚያለማ፤ የሚተክል እና የሚጠግን፤
   
   ለ) በዚህ መመሪያ መሰረት በሚወጣው ሰንጠረዥ መሰረት ተፈላጊውን የኤክሳይዝ ቴምብር የሚያትም እና የሚያከፋፍል፤
   
   ሐ) አግባብነት ያለውን የስርአቱ አካል የሆነ መሳሪያ ለአምራቾች እና ለአስመጪዎች የሚያቀርብ እና የሚጠግን ፤እና

   መ) የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው አስተማማኝ ቦታ አካላዊ ወይም የዲጂታል የኤክሳይዝ ቴምብር ለማተም የሚያገለግል አንድ ማተሚያ ቤት ማቋቋምን ጨምሮ ለታክሱ ባለስልጣን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተዛማጅ የአስተዳደር ስርዓቶችን የሚዘረጋ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመረጠው ኩባንያ በታክስ ባለስልጣኑ ካልታዘዘ በስተቀር በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ማናቸውንም አይነት የኤክሳይዝ ቴምብር ለማተም አይችልም፡፡

3) በኩባንያው እና በሚኒስቴሩ መካከል የሚፈረመው ስምምነት ከሌሎች መካከል ኩባንያው በስራው አጋጣሚ የሚያገኘውን የታክስ ከፋዮች የንግድ

ሚስጥር መጠበቅ የሚገባው መሆኑን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ የታክስ ከፋዮች የንግድ ሚስጥር በአግባቡ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኩባንያው ቦንድ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ ሚኒስቴሩ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

4) በሚኒስቴሩ እና በኩባንያው መካከል በሚደረገው የአገልግሎት ውል በተመለከተው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ፕሮቶኮል እና ስርአት መሰረት ኩባንያው የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልባቸው እቃዎች አግባብነት ያለውን የተለየ መለያ እንዲያወጣ ሚኒስቴሩ መጠየቅ አለበት፡፡

## 10. የኤክሳይዝ ቴምብርን ስለማስረከብ

1) የታክስ ባለስልጣኑ አግባብነት ያለው የስራ ክፍል የሚያስቀምጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የታክስ ባለስልጣኑ ኩባንያው በባለስልጣኑ የተዘረጋውን የአሰራር ስርአት በመከተል የተለየ መለያ ያለው የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲያትም እና በቀጥታ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው እንዲያስረክብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ኩባንያው ከታክስ ባለስልጣኑ የተቀበለውን የሕትመት ትዕዛዝ በ10 (አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲያትም የተመረጠው ኩባንያ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ያተመውን እና ያከፋፈለውን የኤክሳይዝ ቴምብር አይነት እና ብዛት የሚያሳይ መረጃ የታክስ ባለስልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባላስልጣን መስጠት አለበት፡፡

4) የታክስ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት አምራቾች እና አስመጪዎች የወሰዱትን የኤክሳይዝ ቴምብር አጠቃቀም ትክክለኝነት በመከታተል ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 11. የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፍበት ጊዜ እና ቦታ

1) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ቴምብር የሚለጠፈው የታክሱ ባለስልጣን በሚያወጣው አግባብነት ያለው መመሪያ

በሚወስነው ተጨማሪ ዝርዝር መሰረት ሆኖ፤ በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡፡

ሀ) በአገር ውስጥ በሚመረቱ እቃዎች ላይ በማምረቻ ቦታው እንደአግባብነቱ ምርቱ እንደታሸገ በመያዣው ላይ ወዲያውኑ ወይም በማሸጊያው እቃ፤ በእቃው ላይ በሚለጠፍ መግለጫ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ቦታዎች፤

ለ) ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ፤

1) በጉምሩክ ጣቢያ፤
2) አግባብነት ያለው የታክስ ባለስልጣን በሚወስነው ቦታ የጉምሩክ ፎርማሊቲ በተጠናቀቀ በ 5 ቀናት ጊዜ ውስጥ ሲሆን፤ ይህም ቦታ ሚኒስቴሩ ለቁጥጥር አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ተፈላጊ ሁኔታዎች እና ቦንድድ ስለሆነ የእቃ ዝውውር አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች የተመለከተውን የሚከተል መሆን አለበት፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) የተመለከተው ቢኖርም የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ቴምብር እቃዎቹ በሚላኩበት አገር በሚገኝ የማምረቻ ቦታ እንዲለጠፍ ሊያዝ ይችላል፡፡

2) የታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት በእያንዳንዱ መያዣ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ምርት ምንነት ለማወቅ፤ ምርቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር እና የተመረተውን ምርት ሂሳብ ለመመዝገብ የሚያስችል ሊታይ በሚችል ቦታ ሊጠፋ በማይችል ቀለም የዲጂታል ቴምብር እንዲታተምበት ሊያዝ ይችላል፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርት ወይም ወደ አገር የሚያስገባ ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ወይም በመያዣው ላይ የኤክሳይዝ ቴምብሩን እንደለጠፈ ወዲያውኑ የአስተዳደር ስርአቱን በመጠቀም ይህንኑ ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

4) ይህንን መመሪያ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማናቸውም ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡

## 12. የኤክሳይዝ ቴምብርን ተመላሽ ስለማድረግ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች የሚያመርት ወይም ወደአገር የሚያስገባ ማናቸውም ሰው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ጥቅም ላይ ያላዋለውን የታተመ የኤክሳይዝ ቴምብር ለታክሱ ባለስልጣን ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ) አምራቹ የማምረት ስራውን ሲያቋርጥ፤
ለ) የኤክሳይዝ ቴምብሩ ወረቀት ወይም ጥቅሉ ብልሽት ያለበት ከሆነ፤
ሐ) ማስታወቂያ በቀረበበት ወደአገር በሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ እና ወደአገር መግባቱ በተረጋጠው እቃ መካከል ልዩነት ያለ ሲሆን፤
መ) የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ቴምብሩ ጥቅም ላይ እንዳይውል የወሰነ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ የኤክሳይዝ ቴምብር ከሚለጠፍባቸው እቃዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲወጣ በሚኒስቴሩ የተወሰነ ከሆነ፤

2) ኩባንያው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (ሐ) ከተመለከቱት በስተቀር የኤክሳይዝ ቴምብሩ ተመላሽ ከተደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ሰላሳ ቀን ጊዜ ውስጥ አምራቹ ወይም አስመጪው ለመለሰው የታተመ የኤክሳይዝ ቴምብር የከፈለውን ክፍያ መመለስ አለበት፡፡

3) ኩባንያው በሚኒስቴሩ እና በኩባንያው መካከል በተፈረመው ውል የተዘረጋውን የአሰራር ስርአት በመከተል ለታክሱ ባለስልጣን በሚያቀርበው ወቅታዊ ሪፖርት ውስጥ ተመላሽ የተደረገውን የኤክሳይዝ ቴምብር ክፍያ፤ የተሰረዘውን የተለየ መለያ ዝርዝር እና የመሳስሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡፡

4) የታክሱ ባለስልጣን የተሰረዘውን የተለየ መለያ በሚመለከት ክትትል ማድረግ አለበት፡፡ የተሰረዘው የተለየ መለያ በምርቶች ላይ ጥቅም ላይ ውሎ ከተገኘ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

5) የታክሱ ባልስልጣን ተመላሽ በተደረጉ እቃዎች ላይ ለኤክሳይዝ ታክስ አላማ ጥቅም ላይ የዋለውን የታተመ ምልክት ወይም የተለየ መለያ የሚመለከት ስርአት ይዘረጋል፡፡

## 13. የተበላሹ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው የኤክሳይዝ ቴምብሮች

1) ብልሽት የደረሰባቸው የታተሙ ኤክሳይዝ ቴምብሮች የታክስ ባለስልጣኑ ብልሽቱን እስከሚያረጋግጥ ድረስ ተይዘው መቆየት አለባቸው፡፡ ባለስልጣኑ የተበለሹ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ሲያረጋግጥ የባለስልጣኑ ተወካይ በተገኘበት እንዲወገዱ ይደረጋል::
2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ በታክሱ ባለስልጣን ትእዛዝ የተረከባቸውን የኤክሳይዝ ቴምብሮች ሂሳብ ማወራረድ ያልቻለ እንደሆነ ያልተወራረደውን የኤክሳይዝ ቴምብር በሚመለከት የታክሱ ባለስልጣን እንደአግባብነቱ አምራቹ ወይም አስመጪው ባመረታቸው ወይም ወደአገር ባስገባቸው እቃዎች ላይ በእቃዎቹ ምድብ ውስጥ ያለውን ከፍተኛውን የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ፤ የእቃዎቹን ዋጋ እና የእቃዎቹን ብዛት መሰረት በማድረግ የኤክሳይዝ ታክሱን እና ሌሎች ታክሶችን አስልቶ ያስከፍላል፡፡
3) የታክሱ ባለስልጣን ያልተወራረደውን የኤክሳይዝ ቴምብር ስሌት በሚያከናውንበት ጊዜ ለተበለሹ ወይም ጉዳት ለደረሰባቸው የኤክሳይዝ ቴምብሮች ማካካሻ መፍቀድ ያለበት ሲሆን፤ በዚህ አይነት የሚፈቀደው ማካካሻ አምራቹ ወይም አስመጪው ከተረከበው ቴምብር 1% በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

## 14. የኤክሳይዝ ቴምብርን ስለማስተላለፍ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራች ወይም አስመጪ በታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ ሲፈቀድለት በእጁ የሚገኘውን የታተመ የኤክሳይዝ ቴምብር በባለቤትነቱ ስር ለሚገኝ ለሌላ አምራች ወይም አስመጪ ዘርፍ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2) የታክስ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የኤክሳይዝ ቴምብር የሚተላለፍበትን ስርዓት እና የሂሳቡን አመዘጋገብ ይወስናል፡፡

## 15. መዝገቦችን ስለመያዝ

አምራቾች ወይም አስመጪዎች በዚህ ክፍል መሰረት የኤክሳይዝ ቴምብሮችን ከኩባንያው ከተረከቡ በኋላ የሚከተሉትን መዝግበው መያዝ አለባቸው፤

1) ባለፈው ወር መጨረሻ ቀን ድረስ የተከማቹ እና በጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉት የታተሙ ቴምብሮች ብዛት እና አይነት ማጠቃለያ፣
2) በወር ውስጥ ከኩባንያው የተረከቡዋቸውን የታተሙ ቴምብሮች ብዛት እና አይነት ማጠቃለያ፣
3) ሥራ ላይ በማዋል ሂደት ውስጥ የተበላሹት እና ጉዳት የደረሰባቸው የኤክሳይዝ ቴምብሮች ብዛት እና አይነት፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርአት

## 16. የአስተዳደር ስርአት ስለመዘርጋት

በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራች ወይም አስመጪ እንደሁኔታው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሚያመርትበት ወይም ወደአገር ያስገባቸውን እቃዎች በሚያከማችበት ቦታ የአስተዳደር ስርአት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡

## 17. የአስተዳደር ስርአት ይዘት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሰረት የሚዘረጋው የአስተዳደር ስርአት የሚከተሉትን ሊይዝ ይገባል፤

1) የኤክሳይዝ ቴምብርን ትክክለኛነት የሚያጣራ እና የሚያረጋግጥ መሳሪያ፤

2) እያንዳንዱን የኤክሳይዝ ቴምብር ከተለጠፈበት መያዣ ጋር አስተሳስሮ መለየት የሚያስችል መሳሪያ፤

3) የምርት ሂሳብን መመዝገብ የሚያስችል መሳሪያ፤እና

4) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የተለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር መቆጣጠር፣ መመዝገብ፣ መሰነድ እና ለታክስ ባለስልጣኑ መረጃውን ማስተላለፍ የሚያስችል መሳሪያ።

## 18. የአስተዳደር ስርአት ተከላ ማጣጣም

የአስተዳደሩ ስርአት አካል የሆኑ እና በአምራቹ የማምረቻ ቦታ ወይም በአስመጪው ማከማቻ ስፍራ እና በታክስ ባለስልጣኑ ዋና የመረጃ ማእከል እና የአደጋ ማገገሚያ ማዕከል ስርዓት የሚገጠሙ መሳሪያዎች ተከላ፣ የማጣጣም ስራ እና የጥገና ወይም እድሳት ስራ የሚከናወነው የታክሱ ባለስልጣን በሚመድበው ስልጣን የተሰጠው ሰው ተቆጣጣሪነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሰረት በሚመረጠው ኩባንያ አማካኝነት ይሆናል።

## 19. የማልማት እና የመቆጣጠር ተግባር

የታክሱ ባለስልጣን፡

1) ኩባንያው የሚዘረጋው የአስተዳደር ስርአት ሊያከናውነው የሚገባውን ተግባር፣ የደህንነት አጠባበቁን እና ተፈላጊውን የገቢ እና ወጪ ቁጥጥር ስርአት ይወስናል፣

2) የአስተዳደር ስርአቱ በሚዘረጋበት ጊዜ የቁጥጥር እና የክትትል ስራ ያከናውናል።

## 20. የመሳሪያዎች ተከላ እና ሶፍትዌር ልማት

1) የተለየ መለያን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው ሶፍትዌር በታክሱ ባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤት መጫን እና የመተግበሪያ እና የማስተዳደሪያ ሶፍት ዌር ሞጁል የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልባቸው እቃዎች አምራቾች እና አስመጪዎች መስጠት አለባቸው።

2) የአስተዳደር ስርአቱ አካል የሆኑ መሳሪያዎች:

ሀ) በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ በሁሉም የማምረቻ መስመሮች ከእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የምልክት ማተሚያ መሳሪያ ጋር በተጓዳኝ፣

ለ) በታክስ ባለስልጣኑ ማእከላዊ የመቆጣጠሪያ ማእከል እና የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ማዕከል ውስጥ:

መገጠም አለባቸው፡፡

3) ወደአገር ለሚገቡ እቃዎች የሚውሉ የአስተዳደር ስርአቱ አካል የሆኑ መሳሪያዎች የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው አኳኋን ይገጠማሉ፡፡

## 21.የአስተዳደር ስርአቱን ለማሻሻል ወይም በአዲስ ለመተካት ስለሚሰጥ ማስታወቂያ

1) አዲስ ወይም የተሻሻለ የአስተዳደር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን አዲሱ ወይም የተሻሻለው የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ ከሚውልበት ቀን ቢያንስ 30 ቀን አስቀድሞ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፤

ሀ) አዲሱን ወይም የተሻሻለውን የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች፤

ለ) በእያንዳንዱ የምርት ሂደት ላይ ሊደረግ የሚገባውን የማጣጣም ስራ፤

ሐ) የአስተዳደር ስርአቱ አካል ሆነው የሚገጠሙ እና ስራ ላይ የሚውሉ ኮምፒውተሮች እና ሌሎች መሳሪያዎች የሚገጠሙበትን እና ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ፤

መ) አዲሱ ወይም የተሻሻለው የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ የሚውልበትን ቀን፤

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራቾች ወይም አስመጪዎች የኤክሳይዝ ቴምብርን ስራ ላይ ለማዋል፤ ለማሻሻል ወይም ለማጣጣም ለሚውሉ መሳሪያዎች እንዲሁም በእያንዳንዱ የማምረቻ መስመር መሳሪያዎቹ ለሚገጠሙባቸው ቦታዎች የሚያስፈልገውን ወጪ ይሸፍናሉ፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ በመሳሪያዎች ላይ ማስተካከያ እንዲያደርግ ወይም አዲስ ወይም የተሻሻሉ መስሪያዎች ለመግጠም የሚያሰፈልገውን መረጃ እንዲሰጥ በታክሱ

ባለስልጣን ሲጠየቅ ማስተካከያውን ማድረግ ወይም አዲሱ ወይም የተሻሻለው ስርአት ከሚገጠምበት ቀን ሰባት ቀናት አስቀድሞ መረጃውን መስጠት አለበት፡፡

## 22. የማምረቻ መስመር በትክክል የሚሰራ መሆኑን ስለማረጋገጥ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የመሳሪያዎች ተከላ በሚደረግበት ወቅት የማምረቻ መስመሮች በትክክል የሚሰሩ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 23. አገልግሎት መስጠት ያቋረጡ የማምረቻ መስመሮችን ስለማስታወቅ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ አገልግሎት መሰጠት ያቋረጠ የማምረቻ መስመር በሚኖርበት ጊዜ አገልግሎት መስጠት ካቋረጠበት ጊዜ አንስቶ በ24 ሰአት ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባልስልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡ የታክሱ ባልስጣንም ይህንን መስመር በማሸግ መስመሩ የታሸጉ ስለመሆኑ በአስተዳደር ስርአቱ ላይ ይመዘግባል፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የታክሱን ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ የታሸገውን የማምረቻ መስመር በመጠቀም ማምረት አይችልም፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “አገልግሎት ያቋረጠ የማምረቻ መስመር” ማለት በቴክኒክ ችግር፤ በጥሬ እቃ እጥረት፤ ገበያ በመቀዝቀዝ ወይም በሌላ በተመሳሳይ ምክንያት ከ24 ሰአት በላይ ለሆነ ጊዜ ማምረት ያቆመ የማምረቻ መስመር ነው፡፡

## 24. የመሳሪያዎች ደህንነት

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ በስራ ቦታው ለተገጠሙ መሳሪያዎች እና የአስተዳደር ስርአቱ እንክብካቤ የማድረግ እና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የአስተዳደር ስርአቱ የማይሰራ በሚሆንበት ወይም የደህንነት መጠበቂያ

ማሽጊያዎች የመነካካት አደጋ ባጋጠማቸው ጊዜ ይህንኑ በ24 ሰአት ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለበት።

## 25. የመሳሪያዎች እድሳት ወይም ጥገና

1) ኩባንያው የታክሱ ባለስልጣን በሚመድበው ስልጣን በተሰጠው ሰው ተቆጣጣሪነት ስር ሆኖ በአስተዳደር ስርአቱ ላይ እድሳት ወይም ጥገና ማድረግ አለበት።
2) ኩባንያው በአስተዳደር ስርአቱ ላይ እድሳት ወይም ጥገና የሚያከናውኑ ባለሙያዎችን የስም ዝርዝር እና ለስራው ያላቸውን አግባብነት ለታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ ማስታወቅ አለበት።

## 26. ስለማስታወቅ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ፡-

1) ለውጭ ገበያ ወይም ለቀረጥ ነጻ መደብሮች የሚቀርቡትን ጨምሮ የሚያመርታቸው ወይም ወደአገር የሚያስገባቸውን እቃዎች መያዣዎች እና በእነዚህ መያዣዎች ላይ የሚደረገውን መግለጫ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፤
2) አዳዲስ ምርቶችን ማምረት ከመጀመሩ ወይም በነባር ምርቶቹ ላይ የሚደረገውን መግለጫ ወይም ማሸጊያ ከመለወጡ 60 ቀን በፊት አስገዳጅ የሆኑ የጤና ማስጠንቀቂያዎችን ጨምሮ አዳዲስ የምርት አይነቶችን ወይም በነባር የምርት አይነቶች ላይ የተድረገን ለውጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፤
3) አዳዲስ የምርት አይነቶችን ማምረት ከመጀመሩ በፊት የኤክሳይዝ ቴምብር የተለየ መለያ ምልክት የሚታተምበትን ቦታ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።
4) በሚከተሉት ምክንያቶች የአስተዳደር ስርአቱን ከመዘርጋቱ ወይም ከማስወገዱ በፊት ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።
    ሀ) ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ የማምረቻ መስመሮችን ስራ ከማስቀጠሉ፤

ለ) የማምረቻ መስመሮችን ስራ ከማቋረጡ፤

ሐ) በማምረቻ መስመሮች ላይ ጥገና ከማድረጉ ወይም የማምረቻ መስመሮችን ተግባር ከመለወጡ በፊት፤

መ) አዲስ የማምረቻ መስመር ከመዘርጋቱ በፊት፤ ወይም

ሠ) አዲስ የማምረቻ መሳሪያ ከመግዛቱ ወይም የነበረውን የማምረቻ መሳሪያ ከመሸጡ በፊት፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 27. ከቀረጥ ነጻ በሚሸጡ እቃዎች ወይም መያዣዎች ላይ ምልክት ስለማድረግ

1) በአዋጁ ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ የተደረጉ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እቃዎችን መለየት እና መከታተል እንዲቻል በመያዣው ላይ ከታክሱ ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ ምልክት መደረግ አለበት፡፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም በእቃዎቹ ማሸጊያ ላይ የሚደረገው ምልክት፤

ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እቃዎችን በሚመለከት፤ እቃው የሚላክበትን የመጨረሻ አድራሻ፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎችን በሚመለከት "ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል" የሚል ጽሁፍ፤

ሐ) በቀረጥ ነጻ መደብሮች ወይም ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ የሚሸጥ እቃን በሚመለከት " ከቀረጥ ነጻ" የሚል ጽሁፍ፡፡

### 28. የኤክሳይዝ ቴምብር የማይለጠፍባቸው እቃዎች

1) በዚህ መመሪያ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት እቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር አይለጠፍባቸውም፤

ሀ) ለቀረጥ ነጻ መደብሮች እንዲውሉ የሚመረቱ ወይም ወደአገር የሚገቡ ወይም መብቱ የተቋቋመላቸው ሰዎች ከቀረጥ ነጻ መደብር የሚገዙዋቸው እቃዎች;

ለ) በናሙናነት ወደአገር የሚገቡ ኤክሳይዝ ታክስ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው እቃዎች፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) የተመለከቱት እቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ደንብ በተደነገገው መሰረት “ከቀረጥ ነጻ” የሚል ጽሁፍ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
3) የታክሱ ባላስጣን አምራቾች እና አስመጪዎች የኤክሳይዝ ቴምብር ከመለጠፍ ግዴታ ነጻ ሆነው ለገበያ ያዋሉትን እቃዎች ዝርዝር የሚያሳይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማስታወቂያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 29. የኤክሳይዝ ቴምብርን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ

1) የታክሱ ባለስልጣን አምራች፤ አስመጪ፤ ጅምላ ሻጭ፤ቸርቻሪ በአጠቃላይም ህብረተሰቡ የኤክሳይዝ ቴምብር ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት አተገባበሩን እንዲረዳ ለማድረግ ሰፊ የህዝብ ግንኙነት ስራ ማከናወን አለበት፡፡
2) ማናቸውም አምራች፤ አስመጪ፤ አከፋፋይ፤ቸርቻሪ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ማናቸውም ሌላ ሰው እቃዎቹን ከመረከቡ በፊት በእቃዎቹ ላይ የተለጠፈው የኤክሳይዝ ቴምብር ትክክለኛ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡አግባብነት ያለው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ አግባብ ያለውን የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ አኳኋን ይህንን የማረጋገጥ ተግባር ለማከናወን የሚያስችለውን መተግበሪያ የጫነ እና በመደበኛነት የሚጠቀምበት መሆኑን ማስረዳት አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያከፋፍል ወይም በችርቻሮ የሚሸጥ ሰው፡

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሚያመርት ሰው የተሰጠውን የማስረከቢያ ሰነዶችን፤ ደረሰኞችን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን የንግድ ስራውን ያከናውንበታል ተብሎ በተጠቀሰው ቦታ ይዞ ማቆየት፤ እና

ለ) በስራ ቦታው የኤክሳይዝ ቴምብርን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ ብርሃን እንዲኖር የማድረግ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## 30. የኤክሳይዝ ቴምብርን አቅርቦት ስለመከልከል

የታክሱ ባልስልጣን የሚከተሉትን ፈጽሞ የተገኘ አምራች ወይም አስመጪ የኤክሳይዝ ቴምብር እንዳይሰጠው ሊከለክል ይችላል፡፡

1) አስቀድሞ የተሰጠውን የኤክሳይዝ ቴምብር ሂሳብ ያላወራረደ፤

2) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት የኤክሳይዝ ታክስን የማስታወቅ እና የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ፤

## 31. የኤክሳይዝ ቴምብርን፤ መሳሪያዎችን እና እቃዎችን ስለመያዝ

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፤ በጉምሩክ አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ቴምብሮችን፤ መሳሪያዎችን እና እቃዎችን ለመያዝ ይችላል፤

1) የኤክሳይዝ ቴምብርን በሚመለከት፤

ሀ) አስመስሎ የተሰራ ሆኖ ሲገኝ፤
ለ) ለታክሱ ባለስልጣን መመለስ ያለበት ሆኖ ሳለ፤ ያልተመለሰ ሆኖ ሲገኝ፤
ሐ) ከተፈቀደለት ሰው ወጪ በሌላ ሰው ተይዞ ሲገኝ፤

2) በአዋጁ የተደነገገውን ለማያሟላ እቃ ማከማቻ፤ መሸሸጊያ ወይም ማጓጓዣ ውሎ የተገኘን ተሽከርካሪ፤

3) የኤክሳይዝ ቴምብርን አስመስሎ ለመስራት የሚውል መሳሪያ፤

4) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች፤

ሀ) አስመስሎ የተሰራ  የኤክሳይዝ ቴምብር ተለጥፎባቸው የተገኘ እንደሆነ፤
ለ) በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጪ ተገቢ ባልሆነ አኳኋን የኤክሳይዝ ቴምብር ተለጥፎባቸው የተገኘ እንደሆነ፤
ሐ) በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸው የተገኘ እንደሆነ፤

## 32. አስመስለው የተሰሩ የኤክሳይዝ ቴምብሮችን ወይም የተያዙ እቃዎችን ስለማስወገድ

የታክሱ ባልስልጣን አስመስለው የተሰሩ የኢክሳይዝ ቴምብሮችን እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 31 መሰረት የተያዙ ሌሎች እቃዎችን በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ለማስወገድ ይችላል፡፡

## 33. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ማናቸውም አስመጪ፣ አምራች፣ አከፋፋይ፣ቸርቻሪ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ማናቸውም ሌላ ሰው በእጁ የሚገኙትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እና የኤክሳይዝ ቴምብር ያልተለጠፈባቸው ወይም ምልክት ያልተደረገባቸውን ዕቃዎች የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ቴምብር ለማግኘት ማመልከቻ መቀበል መጀመሩን ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር ከ120 ቀናት በኋላ የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸው ወይም ምልክት ሳይደረገባቸው ለገበያ ማዋል አይችልም፡፡
2. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መኖሩ ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 34. የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድህረ-ገፀ ከተጫነበትቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 2016 ኣ.ም

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

Uploaded on the website of the Ministry of Finance on 12 June 2024.